# የስደት ዘመቻ

ከድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ
zeaddisu_gebeya@yahoo.com

ተማሪ ወታደሩ
ምሑር ጀኔራሉ
ጋዜጠኛ አርታዒ
ሊቃውንቱ ሁሉ
ሥቃይ መከራውን
ግፋን ስላልቻሉ
በትጥቅ በድርጅት
ከሩቅ ሊታገሉ
ያሳዳጁን መንገድ
ታሪክ ሊከተሉ
በባሌ በቦሌ
ፈጥነው ይተማሉ

ርግጫው ሲበዛ
ዱላው ሲሰለቸው
ወጣ ብሎ መግባት
ካድሬው ሲወጥረው
ቀበሌው ወረዳው
ሲከፋ መከራው
ሓቀኛ ከሃዲው
ሲዛባ ስያሜው
ጉዞውን መንገዱን
ይርዳችሁ ጨርቅ ያርገው
ምክሩን ተቀብሎ
ጉዞውን አስነካው
በባሕር በጠረፍ
ወገኔ አቀጠነው
የተከፋ ብዙ
ጎርፉን ማን ሊያቆመው

የሰማውን ሊጽፍ
ያየውን ሊዘግብ
እውነትን ሊዘክር
ሊናገር ሊከትብ
ጎንበስ ቀና ብሎ
ዋቢ ሲሰበስብ

እሥር ጉስቁልና
ሲያመጣ መደብደብ
ልብ ሕይወት ጠየቀ
ሓቅን ለመከተብ
ሃገር ጥሎ መሸሽ
አወይ ስደት መራብ

ነገሩን ጠንቅቀው
ለማጤን የቻሉ
የሥልጣን ምሰሶ
ዲፕሎማት ሁሉ
የመርከቧን መስጠም
መረዳት ሲችሉ
ከመሞት መሰንበት
ብልህ ነው እያሉ
ከዱለኛው ግዛት
ፈጥነው ይሸሻሉ
የስደትን ዕጣ
ሁሉም ሊቀበሉ
የሕይወት-አድን ጀልባ
ዘለው ተካፈሉ
ወዳጅም ጠላትም
አብረው ኮበለሉ

የተከፋው ምድር
እንዲያድር በሰላም
የተጎዳው ወገን
እስኪመለስ ሁሉም
የተራበው በልቶ
የበላው እስኪያልም
በርቱ ቶሎ ቶሎ
ወዳጅም ጠላትም
ሰባራዋ መርከብ
በአስቸኳይ ትስጠም

**************************

© ድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ
መስከረም 1999
zeaddisu_gebeya@yahoo.com
September 2006